# መጽሐፈ ጨዋታ።

## ሥጋዊ ፡ ወመንፈሳዊ።

በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡

ከዘነብ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ተጻፈ ።


፪ኛ ፡ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ፡ም ፡ በተስፋ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ፡ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ

፩ኛ ፡ በ፲፱፻፳፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በጎሀ ፥ ጽባሕ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ

አዲስ ፡ አበባ ።



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# መጽሐፈ ጨዋታ።

## ሥጋዊ ወመንፈሳዊ።

# ማውጫ

መጽሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ።......5
ክፍል ፩። ......5
ክፍል ፪።......7
ክፍል ፫።......8
ክፍል ፬።......10
መጽሐፈ ጨዋታ መንፈሳዊ ፡......16
ክፍል ፩።......16
መጽሐፈ ጨዋታ ወንጌላዊ።......20
ክፍል ፪።......20
ክፍል ፫።......21
ክፍል ፬።......21
ክፍል ፭።......22
ክፍል ፮።......24
ክፍል ፯።......26
ክፍል ፰።......27
ክፍል ፱።......29
ክፍል ፲።......31
ክፍል ፲፩።......32

## መግለጫ ።

ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ጨዋታ ፡ ሥጋዊ ፡ ወመንፈሳዊ ፡ በአፄ ቴዎድሮስ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፲፰፻፶፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ዘነብ ፡ የተባለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የጻፈው ፡ ነው ። ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ ተወጣጥቶ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ፡

በሥጋዊም ፡ ጠቃሚ ፡ የሆኑ ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ ስላሉበት ፡ መልካም ፡ መጽሐፍ ፡ ስለሆነ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ከዚያን ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በብራናና ፡ በወረቀት ፡ እያጸፉ ፡ ራሳቸው ፡ እያነበቡ ፡ ለልጆቻቸውም ፡ አእያስተማሩ ፡ ሲጠቀሙበት ፡ (ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፳፬ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በጎህ ፥ ጽባሕ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታትሞ ፡ ለሕዝብ ፡ ሳይዳረስ ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረበት ፡ ዘመን ፡ ተዘርፎና ፡ ተቃጥሎ በክኖ ፡ ጠፋ ። ይህን ፡ ጠቃሚ ፡ ፍሬ ነገር ፡ ያለበትን ፡ መጽሐፍ ፡ የአሁን ፥ ወጣቶች ፡ አንበው ፡ እንዲጠቀሙበት ፣ ታተመ ።

አዲስ ፡ አበባ ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡
ተስፋ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡ ዘብሔረ ፡ ቡልጋ ።

# መጽሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ።

## ክፍል ፩።

እግዚአብሔር እስቲሻር ሚካኤል እስቲሞት ምነው በኖርሁኝ። ገብርኤል ሲያንቀላፋ ሩፋኤል ሲደክም ሐሰተኛው ዲያቢሎስ ንስሐ ይገባል።

ክረምት ሲመጣ ሰማይ እንዲከብድ የጠሉትም ሰው ሲመጣ እንደዚያ ይከብዳል። ዘወትር ከሚያጋድል አህያ ተሸክሞ መሄድ ይሻላል። ከሚያስተካክል መላከተኛ የማለዳ ወፍ ትሻላለች ምነው ቢሉ ንጋቱን ትነግራለችና።

ደንጋይና ጭቃ ቢቀባጠሉ ታላቅ ቤት ረጅም ቅጥር ይሆናሉ እናንተም መሬታውያን ሰዎች እንደዚህ ብትረዳዱ ጥበባችሁና ኃይላችሁ ከሰማይ በደረሰ።

ኮሶና ክረምት ፊት ይመራል ኋላ ግን ደስ ያሰኛል። ድሪ ምንድር ነው ገንዘብን ለመቆራኘት የተሠራ ሰንሰለት ነው። እሬት መብላት ቢለመድ ባልተለቀቀም ነበር ዝሙትም ላለመደው ሰው እንደዚህ ነው።

ጣዝማ እጅግ ብልህ ናት መሬት ቀዳ ገብታ እንደዚያ ያለ መድኃኒት የሚሆን ማር ትሠራለች። ምነው እናንተ ሰዎች ወይ ከፈጣሪ ወይም ከሰው ብልሀትን አትፈልጉምን።

የምሥራች ከሩቅ አገር በመጣ ጊዜ የሰው ልብ በደስታ ባሕር ይሰጥማል። እርጎን ከፍቶ ቢተውት ዝንብና ድመት ይጫወትበታል አገርንም አቅንቶ ሰው ካላስቀመጡበት ተመልሶ ዱር ይሆናል።

ባባቱ የሚኮራ ሰው ጅል ነው የሰው አባቱ አንድ አዳም አይደለምን። ሴትን ወንድ እንድ ጊዜ ይደርስባታል መንታ ትወልዳለች እህልም አንዲት ፍሬ ተዘርታ ብዙ ታፈራለች ይህ ነገር ከቶ እንዴት ነው እንጃ ማን ያውቀዋል ያ የጠቢቦች ጠቢብ ያወቀው እንደሆነ ነው እንጂ።

ፈረስ በብረት ልጓም ይገታል የሕዝብም ልጓሙ ንጉሥ ነው መቃብር መልካም ጐታ ነው ብስሉንና ጥሬውን ይከታልና። ወዳጅ ቢወዱት ይወዳል መሬትም ቢበሉት ይበላል።

በርበሬ ላይን ቀይ ሆኖ ይታያል ምነው ቢሉ በብልሐት ገብቶ ሊለበልብ። ክፉ ሰውም ቀስ ብሎ ገብቶ ኋላ ነገሩን ያመጣል።

ቸር ሰው ለወዳጁ ጠጅ ነው ፍቅሩ ያሰክራልና። ዝናም ከዘነመ በኋላ ቡቃያ ያበቅላል ንጉሥም ከወደዱ በኋላ ይሾማል።

ሸክላ እጅግ ክፉ ነው ወሀ አርሶ አሠርቶት መከታ እየሆነ እሳትን ያስወጋዋል። ክፉም ሰው እንደዚያ ነው። ወንፊት ዱቄትን እንዲነፋ ዘርዛራም ሸማ ጠጅን እንዲያወርድ ባለቤቱም ያልቻለውን ምሥጢር ሌላው ሰው አይችለውም።

ቅቤ ካይብና ካጓት እንዲለይ በላይም እንዲሆን ጻድቅም ሰው እንደዚያ ነው።

## ክፍል ፪።

ደመና ሰማይን እንዲሸፍነው ንጉሥም በሠራዊቱ እንደዚያ ነው። ሳማና አብላሊት ለምለም መስለው እንዲለበልቡ መናፍቃንም ሲቀርቧቸው እንደዚያው ናቸው።

በቀስታና በዝግታ የተበጀ መዘውር ኋላ ጉልበት ይሆናል። ወረቀት መልካም እርሻ ነው ብዙ ነገር ይዘራልና። ጐታም አይሻ እርሱ ከቶት ይኖራልና።

ማር ሁለት ጊዜ ያገለግላል አንድ ጊዜ መጠጥ አንድ ጊዜ መብራት ሆኖ። ምነው ቢሉ የብልሕ ሥራ ነውና አሰርም የለው።

ሕዝብና ሕዝብ ደጋን ቆላ ናቸው። ንጉሥ ግን ገበያ ነው ሁሉን ያገናኛልና። ሸክላ ከተሰበረ በኋላ ገል ነው። መኳንንትም ለተሻሩ በኋላ ሕዝብ ናቸው።

ክፉ ሰው ሸንቱን በሸነ ጊዜ ኋላ ጉንፋን ይሆናል ምነው ቢሉ ግብሩ ተጉድፍ የተወሐደ ነውና ማርና እሬትን ቢመዝኑ ማን ይደፋል እሬት ምነው ቢሉ ክፉ መራራ ነውና።

ከብዙ ቀን ደስታ ያንድ ቀን መከራ ይበልጣል። ንጉሥ ምሰሶ ነው ሠራዊት ግድግዳ ናቸው። መኳንንት ግን ማገር ናቸው ለንቋጣ ልጡ እንዲማልግ እንጨቱም ቀሊል እንደሆነ ወስላታም ወዳጅ እንደዚያ ነው።

ጨው በዓለሙ ሁሉ ይዞራል ምናልባት ሰልችቶት ይተውኛል ብሎ ነውን ከሬት ጋራ ይጋባ እንደሆነ ነው እንጂ የሚለቀው የለም።

አንድ ዓይንና አንድ ዓይን ያላቸው ተጋብተው ሁለት ዓይን ያለው ልጅ ወለዱ ይህ ነገር ምንድር ነው አንዱ ካባቱ አንዱ ከናቱ ነዋ። የዚህ ዓለም ትርፉ ምንድር ነው መብላት መጠጣት ጥጋብና ኩራት ነው። ኩራት ምንድር ነው እንደርሱ ሆኖ የተፈጠረውን ሰው መናቅ ነው።

ሰው ፍሪዳን አብልቶ አብልቶ ያሰባዋል በመጨረሻውም ይበላዋል። ምነው ቢሉ አብልቶ መብላት እንጂ ገባያ ነው። ወርቅ ቢያብረቀርቅ ብር ያብለጨልጫል ምነው እናንተ ቢያብረቀርቅ ብር ያብለጨልጫል ምነው እናንተ መናፍቃን ጥቂት ጥቂት ብልሐት አታዋጡምን።

የዝንብ ብልሐቷ ምንድር ነው ሌላው የሠራውን መብላት ነው። ሰነፎች ሰዎችም እንደዚሁ ሌላ ሰው የሠራውን መብላት ይወዳሉ።

ደሀ ከመሆን ሀብታም መሆን ይሻላል ምነው ቢሉ አይቸግርምና። በምድር ከመኖር በሰማይ መኖር ይሻላል ምነው ቢሉ የዚህ ዓለም መከራው ብዙ ነውና።

ከባለጌ ፍቅር የንጉሥ ቁጣ ይሻላል የረሀብ ጌትነቱ መቼ ነው እህል በታጣ ጊዜ ነው ምነው ቢሉ የሌላውን አምጡ ይላልና። የማጣትስ ጌትነቱ መቼ ነው ፡ የፈለጉት ነገር በታጣ ጊዜ ነው። የጥጋቡስ ጌትነቱ መቼ ነው መብልና መጠጥ በተገኘ ጊዜ ነው። የመብላትስ ትርፉ ምንድር ነው ጥጋብ ነው።

## ክፍል ፫።

ሥራ ሳትሠራ በስንፍና ካልጋ ላይ ተቀምጣ ከምትውል ሴት ገጣባ አህያ ይሻላል ምነው ቢሉ ጭኖ ያበላልና።

ጉጠት የበረደውንና የጋለውን ብረት እንዲይዝ ፡ እብድ ሰውም እንደዚህ ነው። መቃጥንና ብልህ መላክተኛ አንድ ናቸው ምነው ቢሉ ደጎና መስለው ስበው ያስገድዳሉና።

አንስሶች ሁሉ የሚበሉት አንድ ሣር ነው ምነው ፋንድያቸውን ተለዋወጠ። ሰዎችም አባታቸው አንድ አዳም ሲሆን ምነው ዓይነታቸው በዛ።

ንጉሥ የቃጣውን ጽዋ በጠጣህ ጊዜ ተጠንቀቅ ፡ ሌሊት እንዳያነዝዝህ። አቀፈ አዘለ ማለት ምንድር ነው ስሙና አጠራሩ በየራሱ ቢሆን ነው እንጂ ሁሉም ተሸከመ ማለት ነው።

ሰይጣን ጋኔን ዘር ማለት ምንድር ነው ስሙ መለዋወጡ ነው ስሙ መለዋወጡ ነው እንጂ ሁሉም ጋኔን ነው።

የውሻ ጅራቱ ወደላይ እንዲቆም የሹመት ፈላጊም ልብ እንደዚያ ነው። መርፌ ሸማን የሚወጋው ምን እጠቀም ብሎ ነው በኋላም እንጂ ፈትል ተከትሎታል እነዚያ እንዲጠቃቀሙ አያውቅምን እንደዚህ ያለ ሞኝ የፊቱን እንጂ የኋላውን የማያይ ይልቁንስ የርሱን ቀዳዳ በጠቀመ።

ውሽማ በሴት ዘንድ ማር ነው ባል ግን ሬት ነው ስለዚህ የስስት መልክና የሴት ልብ አንድ ነው፣ ምነው ቢሉ ወዲያው ይለዋወጣልና።

ብር አሁን ምን ኃጢአት ውሎ ይሆን ሲሸጥ ሲሸጥ ኖሮ ከእሳት የሚገባ፣ ለካ አታውቅምን ፡ ቤል ጀምሮ እስከ ይሁዳ ይኖራል እርሱ እሳት ያገባል ማን ይግባለት።

አገር ካየር ሲርቅ ቆላ ይሆናል ፡ ካየር ቢቀርብ ግን ደጋ ስለሆነ ውርጭ በረዶ ይሆናል ፡ እንደዚሁም ከንጉሥ የቀረበ ልምላሜ ያገኛል ከንጉሥ የራቀ ደሀ ይሆናል። እሳትንና ንጉሥን እጅግ አትራቅ እንዳይበርድህ እጅግም አትቅረብ እንዳይፈጅህ።

## ክፍል ፬።

ከገንዘብ መልካም ማነው ወርቅ ነገርንና ጥልን የሚያርቅ ማነው ዕርቅ ኑዋሪስ ማነው ጽድቅ ሣቅ ምንድር ነው የደስታ ሳንቃ ነው ዘፈን ምንድር ነው የደስታ ማለፊያ ነው እልልታ ምንድር ነው የደስታ መክፈያ አዋጅ ነው።

ልቅሶ ምንድር ነው የኃዘን ወንዝ ነው። ትካዜ ምንድር ነው የመከፋት ጓዝ ነው።

እስስት ስትጐተት እንደምትጠላ ሁልጊዜም የሚለውን ሰው እንደዚያ ነው። ባለጌ በበቅሎ ላይ ቢሄድ ወደ ሰማይ የወጣ ይመለዋል። ተኩሩ ባሪያ ወደል ውሻ ይሻላል። ምነው ቢሉ ጌታውን ባዬ ጊዜ ጅራቱን ይቆላልና።

ተጌጥ መልካም ማነው ወርቅና ብር። ለሰልፍስ መልካም ማነው ባሩድና አረር። ተገላጋይ መልካም ማነው አስቀድሞ ማፈር ከመብልስ ጣፋጭ ማነው ማርና ሱካር ሰብሳቢስ ማነው መቃብር።

ለሰውስ መልካም ማነው አገር ለወገብስ መልካም ማነው ዝናር። ቀዝቃዛስ ማነው በረዶ። ድንገተኛ ማነው አግኝቶ ማጣት ተንቆ መኖር። ውርጭስ ማነው ሲበሉ ማየት። መታረዝ ምንድር ነው ተሹሞ መሻር። ብርድ ምንድር ነው የቅናት ገዢ የልብስ ዘርፍ ማነው ጭፍራ። ከተራራ ማነው ይውላል ንጉሥና መነጽር። ካረህ ማን ይውላል ነፍጠኛ። ከሜዳ ማን ይውላል ፈረሰኛ።

ደመና ብልህ ነው። ወሀን ከምድር አውጥቶ ምድርን ያጠጣልና። ምነው ነገሥታትስ የደጋውን ለቆላ የቆላውን ለደጋ አያደርጉትምን። የፍየል ንጉሥ ነምር ነው የበግ ንጉሥ ተኵላ ነው። ያህያ ንጉሥ ጅብ ነው። ያራዊት ንጉሥ አንበሳ ነው። የክፋት ምንጭ ዲያቢሎስ ነው።

እባብ የሰይጣን በቅሎ ናት። ፋደት ውሻ በመጣበት ጊዜ ትፈሳበታለች። ተመልሶ እየጮኸ ይሸሻል። ያም ስፍራ እስከ ብዙ ቀን ድረስ እየገማ ይኖራል። ጻድቃንም የእግዚአብሔርን ነገር ሊያስተምሩ በጀመሩ ጊዜ ሰይጣን ክፉ ነገር በመካከላቸው አምጥቶ እንደውሻ ያባርራቸዋል።

ንጉሥ ኮርቶ የደኃውን ጩኸት ባይሰማ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለተናቀ ሰው ይሰጥበታል። መኰንን ቢኮራ ይሞታል ወይም ይታሰራል። ዘመን ያነሣው ታላቅ ዜማ እንቅርት ያፈርጣል።

ምላሰኛ ሴት ጠብ ከጐረቤት ባሰማች ጊዜ ምላሷን መለመጥ ትጀምራለች። ፍቅር ዘውድ ነው። መልካም ጠባይ ዝናር ነው። ትሕትናም ጫማ ነው። ጥል ባሕር ነው ፍቅር ግን መርከብ ነው። መልካም ምላስ መልሕቅ ነው።

ደመና በቦረ ጊዜ ጨው ይቀልጣል የሰው ኃጢአት በበዛች ጊዜ የእግዚአብሔር ረድኤት ይርቃል። የሰው ገንዘብ የለመደ ሹም ያህያ ሥጋ የለመደ ጅብ አይቻልም። መጋዝ ቢከረክር ምሣር ይፈልጣል። ምነው አናንተ ሰዎች እንዳቅም እንዳቅማችሁ ብልሐት አትፈልጉምን። ነጋዴ ቢያረጅ ከገበያ ሂዶ ይጐለታል። ሌባ ቢያረጅ ልብሱን ተገፎ ተአልጋ ውስጥ ይሰወራል።

አመድ የእንጨት ሬሳ፥ ነው ፡ ማን ይቀረዋል ነፋስ። ዘወትር እየቀባጠረ ከሚጸልይ ሰው ፡ ሲነጋ የሚንጫጩ ወፎች ይሻላሉ። መልካም ጠጅ ቢጠጡት ጊዜ አካል ሁሉ ብርሃን ይሆናል። ስካር ምሽት በመጣ ጊዜ ሁሉ ጨለማ ይሆናል።

ጥበብ ለምን ትፈልጓታላችሁ ፡ ከገበያ አትገዛ ፡ ከምድር አትበቅል። ከኪሩቤል ጀርባ ካለው ከሕይወት ምንጭ በሃይማኖት ብርጭቆ ቅዱ።

በሬ በቅልጥሙ ቅባቱን ይዞት ይኖራል። ገና ኋላ ለቁርበቱ ማልፊያ ይሆነኛል ብሎ ነውን። ያዳምም ልጆች እንደዚሁ ለተዝካራቸው ያኖራሉ። ምነው ዓይናቸው ሲያይ ቢሰጡት ይኰነኑ ይሆን።

እግዚአብሔር በጥበብ ሁሉን ሁለት ሁለት አድርጎ ፈጠረ። አስተውል ሰማይንና ምድርን፣ ፀሐይንና ጨረቃን፣ በጋንና ክረምትን ቀንንና ሌሊትን፣ ሰውንና መላእክትን ፡ አዳምንና ሔዋንን ፡ ጽድቅንና ኵነኔን ፡ ይህችን ዓለምና የወዲያኛዪቱን ዓለም።

ከስካር ጋራ አንድ ቀን ከመዋል አርባ ቀን መጾም ይሻላል። አሸን በክረምት ወራት በአንዲት ሰዓት ከጕድጓዱ ወጥቶ በክፍንፉ እንዲበር በ፪ተኛውም ሰዓት ክንፉ ረግፎ በእግሩ እንዲሄድ ወፍም እንደሚባለው የዚህም ዓለም ተድላውና ደስታው ክብሩም ዕድሜውም እንደዚያ ነው።

የእሳት ራት ዙራ ፈልጋ ከእሳት እንደምትገባ ኃጥአንም ዲያቢሎስን ዙረው ፈልገው ገሃነመ እሳት ይገባሉ። መልካምን መብል መልካምን መጠጥ ፡ ዓለምንም ሁሉ ቢወዱት ምን ይሆናል። ሞት ድንገት መጥቶ አስጨንቆ በግድ ይወስዳልና።

እሳት በእንጨት ነዶ እንዲገለጥ፣ እግዚአብሔርም በጻድቃን ላይ እንደዚያ ነው። ጉሽ ጠላና ያልፈላ ወጥ ልብ እንዲያስተኩስ ፡ ሳይሰፍሩ ሳይቆጥሩ ያኖሩትም ገንዘብ እንደዚያ ነው ፡ ሰውንም ያሳማል።

መሬት መሬትን ይበላዋል። የሴት ልብ ቀላይ ባሕር ነው አቅፏት ከሚተኛ በቀር ማን ያውቀዋል። በመዘውር ይዘው ሲያሠሯቸው ይኖራሉ። ደመወዛቸውን እንኳ አይሰጧቸውም አይኰነኑ ይሆንን።

ኮምጣጣ ጠላ መጠጣት ጅማት ያሰቅቃል። የክፉ ሰውም ነገር አንጀት ይበጥሳል። መርከብ በባሕር መካከል ሲሄድ ድንገት ድንጋይ እንዲያፈርሰው ፡ ንጉሥም በሠራዊቱ ላይ እንደዚያ ነው መንግሥቱን በበደለ ጊዜ።

እንጨትና ሣር ዝናም አብቅሏቸው አንዱ ባጥ አንዱ ግድግዳ እየሆኑ አናስገባ ይሉታል። መናፍቃንም የፈጠራቸውን እግዚአብሔርን ትተው ለፍጡር ይሰግዳሉ።

ነገሥታትና መምህራን እንደ ውሀ መልካም ቢሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ ወንጌል በዓለሙ ሁሉ በተሰበከ ነበር። የውሀም መልካምነቱ እንደዚህ ነው ፡ ከምድር ላይ በፈሰሰ ጊዜ ሁሉን አብቅሎ ምግብና ልብስ ይሆናል። ዶቄቱን አርሶ እንጀራ ያደርገዋል ፡ የደረቀውን እርሾ ለስላሳ ያደርገዋል። ያደፈውን አጥቦ ንጹሕ ያደርገዋል። ከጠጅና ከጠላ ውስጥ ገብቶ ጣማቸውንና ሽታቸውን ያሳምረዋል መምህራንም እንደዚህ ቢሆኑ ዓለሙ ሁሉ አንድ አካል አንድ አምሳል አንድ ነፍስ በሆነ ነበር።

ዓሣ ከውሀ ውስጥ ከመኖር መሬትና ደንጊያ ከመላስ ከኛ ዘንድ መጥቶ ጨውና ቅቤ አይበላምን ፡ ቆቅስ ከኛ ዘንድ መጥታ ብትመረቅ ሀብት አግኝታ እንጀራ ባልበላችምን ጥሬ ሲፈልጉ ከመኖር።

ዘንዶ ቢረዝም አሁን ምን ይጠቀማል የሰይጣን፥ ማደሪያ ሆነ እንጂ እግርና እጅ እንኳ የለውም። መናፍቃንስ ቢበዙ ብልሀት ሳይኖራቸው ምን ይሆናሉ። እናንተ ሰነፎች ድንቁርናን ከማይመለስበት ሽጡት የሰነበተ እንደሆነ ይገድላችኋልና።

ስብ ቢያጤሱት ይሸታል ብልሀትም ቢያበዙት ያከብራል። ሰልፍን መነኩሴ ያውቃል ዝንብን ሁል ጊዜ በጭራ ዓይን ዓይኗን ይላታልና። ዕውር ሰው አንድ ቀን መልካም ወጥ የቀመሰ እንደ ሆነ ሁል ጊዜ ያው ይመስለዋል።

አንበሳ እግዚአብሔር የፈጠረውን ምን ቸገረኝ ብሎ ነፍስ ካልገደለ የማይበላ።

ላምና በግ ጠጉርና ቁርበት ለብሶ ከመኖሩ ሸማና ግምጃ ከለበሰው ውስጥ ገብተው በቅቤና በጨው ታፍኖ መኖር አይሻላቸውምን። ዶሮስ

ይህ ኮስኳስ ሽቀናም ጠጉር ምን ይሆናታል ድልህና ቅቤ አጥግቤ በሞቀ ወህ አጥቤ ከሚሞቅ ቦታ ብከታት አይሻላትምን።

ዓሣስ ከውሀ ውስጥ መኖሩ ምን እጠቀም ብሎ ነው ፡ እንደኔስ ቢሆን ከብርድ ስፍራ መኖር እጅግ ያሳዝነኛል አጥቤ እንዲሞቀው ከእሳት ዳር ባደረኩት ነበር። በወደደው ልክ ጨውና ቅባኑግም አጠግበው ነበር።

ሎሚ ሲያብብ ይኖራል ፡ መልካም ይሸታል መኮምጠጡን ካልተወ ግን ምን ይሆናል ፊት ያጠቁራልና። ጅብ ያህያ ሥጋ የጠገበ ጊዜ ጨኸቱ ካገር አያስቀምጥም።

የነብር ቁርበት ከበረት ቢሰቀል ፍየሎች ይደገድጋሉ። ብርቱም ንጉሥ በተነሣ ጊዜ መናፍቃን ይታወካሉ። የጐመን ዘር ቢዘሩት ሰናፍጭ አይሆንም፣ ሰውንም አንተ ባሪያ አንተ ጋላ ብሎ ቢሰድቡት የአዳም ልጅ መሆኑን አይተውም።

ፍቅር ቢያረጅ ቅርፍት ይሆናል (ይይዛል) ምነው ቢሉ ተቀርፎ ሊወድቅ ፡ ከመልካም ከታላቅ ወንዝ ከለመለመ ብትደርስ ተጠንቀቅ ከዚያ የሚመጣው ብዙ ነውና።

መልካም ቆንጆ አመንዝራ ሴት ካለችበት ቤት አትግባ ፡ በከንቱ እንዳትሞ። ሴት ከመሆን ወንድ መሆን ይሻላል። እንስሳ ከመሆን ሰው መሆን ይሻላል። ደንቆሮ ከመሆን ብልህ መሆን ይሻላል።

መላጣ ሰው የፀሐይ ወዳጅ ነው። ያለውን ሁሉ ያሳያታልና። ጠጉራም ሰው ያስቀይማታል ምነው ቢሉ ጠጉሩን ያንጨፈርርባታልና። ነጭ ሽንኩርት ምነው ይሸታል ይተኩሳል ቢሉ እርሱማ የጠባዩን ክፋት አውቆ እራሱን ወደ ምድር ቀብሮ እኖራለሁ ቢል ና ውጣ እያላችሁ እናንተ ብታሳዱት ምን ትጠቀማላችሁ።

ማሽላን ወፎች እራስ እራሱን ሲሉት አይቶ ባቄላ ፍሬውን በጒኑ አዝሎ ከንፋን አልብሶ ይኖራልና። ብልህ ሰው በጨነቀው ጊዜ ሞኝ ይሆናል።

ገዴ አሞራ እርሷ ያልገደለችውን ሥጋ አትበላም መልካምም ሰው ያለገንዘቡ አይነካም። ረሀብ ውሎውና አዳሩ ከማነው ሥራ ከማይወድ ከኩሩ ሰው ጋራ ነው። ጥጋቡ ውሎውና አዳሩ ከማነው ከሠራተኛና ከቸር ሰው ጋራ ነው። ሰይጣንስ አዳሩና ውሎው ከማን ጋራ ከልበ ጠማማና ከዕቡይ ሰው ጋራ ነው። ካለውና ከሞተው ሰው ማን ይበልጣል የሚምለውንና የሚገዘተውን ሰው ጨምሮ የሞተው ይበልጣል። ስግብግብ ሰው ለመብል የሚጣደፍ ሆዱ አምላኩ ነውና ታላቅ ጉርሻ ጒርሶ አንቆት ወይም ሆዱን ነፍቶት ቁንጣን ይገድለዋል።

ጨለማ እጅግ ጠላታችን ሆነ ገና ሳንተያይ ፊቱን ያጠቁራልና ሥራችሁንም አትሥሩ ይላል እርሱ የሰንበት ሹም መሆኑ ነውን እርስ በርሳችሁም አትተያዩ ይላል እግዚአብሔር ይመስገን ዘመድ አላጣንም የብርሃን ልጆች ነነ። ሁሉንም እናሳድምና ፀሐይና ጨረቃን ከዋክብትንም በፊት ግጠሙት ብለን በኋላው እሳትን እንልቀቅበት። ዓይናችንም ዘወትር ጠላቱን ከማየት ይረፍ።

ሱፍ አበባውን አሳምሮ አሾሁን አጥሮ ይኖራል። ምነው ቢሉ የአዳም ልጆች ጉምጁዎች ናቸውና ዘለው እንዲይዙት ነው። አሁን ቢጮሁ አጣጥና ግራር ባልረዱዋቸውምን እረ ገና እነዚህ ፍሬ ቢሶች ተገትረው የቀሩትን ምን ጣም አላቸው ብለህ ነው። ኮሞር ገንዘብ ሲወድ ነፍስም የለው ዘወትር የሚገኘው ከወርቅ ቤት ነውና ያጠመደ አያጣውም። ሥጋም ፍራቱን እጅግ አበዛው ከታረደ በኋላ ምን ያንቀጠቅጠዋል ምንስ ያንበደብደዋል።

# መጽሐፈ ጨዋታ መንፈሳዊ ፡

## ክፍል ፩።

ቅቤ ለመጽሐፍ ዘመዱ አይደለም ፡ መጽሐፍ ግን ለሰው ቅቤ ነው አታክልት ሆኖ ካላፈራ ሰው ሆኖ እግዚአብሔርን ካልፈራ መቆረጥ አይቀርለትም። ኮትኳችና አራሚ የሌለው አትክልት አይረባም ንጉሥና መምሕር የሌላትም አገር እንደዚህ ናት ኃጢአት አትሠራ ደስ ይላታል ፡ ኋላ ግን ፍሬ ስታፈራ ፍሬዋ እሬት ይሆናል።

ከረጢት መስፋቱ ለወርቅ መያዛ ነው የሰው ልብም መፈጠሩ ክፉና በጎ ለማወቅ ነው። የጃርት ልብሷ እሾህ ነው፥ የዲያቢሎስም ልብሱ ክፋት ነው።

ሸንኩርትና ድንች ፍሬያቸው በሥራቸው እንደ ሆነ ፡ ጻድቃንም በሥራቸው ለማፍራት የአምላካቸውን ነገር በልባቸው ይተክላሉ።

በገና ሆዱ አንድ ሆኖ ለወፍራሙም ለቀጭኑም እንደ ጠባያቸው እንደሚጮህ እግዚአብሔርም አንድ ሲሆን ለፍጥረቱ ሁሉ እንደጠባይ እንደ ጠባዩ ይሰጠዋል።

የተምር ፍሬ እንዲጣፍጥ የጻድቃንም ሥራ እንደዚያ ነው ቅል በዝናም ይበቅላል ሸክላም በውሀ ይሠራል ፡ ኋላ ግን ሁለቱም ለወሀ ማደሪያ ይሆናሉ።

ሰውንም እግዚአብሐር ከፈጠረው በኋላ መልካም ሰው የሆነ እንደሆነ ማደሪያው ያደርገዋል። መሳል መልካም ነው ብረትን ይስለዋልና መሐፍም መልካም ነው ልብን ያበራዋልና።

እግዚአብሔር እጅግ አረጃ ዘመኑንም የሚያውቀው ታጣ። መጽሐፍ መነጽር ነው ለሚመለከተው ሰው ከሩቅ ያሳያልና። ሰነፍ ሰው በሰው

ይታመናል ኋላም ተመልሶ ጠላት ይሆነዋልና ምንም አያገኝም እግዚአብሔርን ግን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉን ያገኛል።

በጥቂት ደመና የደጋ መሬት በረዶ እንደ ሚያፈላ እግዚአብሔርንም በማይፈራ ሰው መከራ ድንገት ይደርስበታል።

ነብር የፍየልን ፡ ተኵላ በግን ፡ ጅብ አህያን ሞጭሞጭላ (ምጥማጥ) ዶሮን እንደሚፈልጉ ዲያቢሎስም የአዳምን ልጆች እንደዚያ ይፈልጋቸዋል።

የወጥ ማጣፈጫው ምንድር ነው ጨውና ቅቤ የሰውም ማጣፈጫ ሃይማኖትና ምግባር ነው። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከማፍረስ እሬት መብላት ይሻላል። ምነው ቢሉ በውሀና በማር ይሟሻልና። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ግን ያፈረሰ ዘለዓለም እንደ መረረው ፡ ይኖራል።

እግዚአብሔር አብ ጣት ነው እግዚአብሔር ወልድ ብዕር ነው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀለም ነው ሰማይና ምድር ወረቀት ናቸው። ፊደሉም ፍጥረት ነው። እግዚአብሔር አብም በቃሉ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ያለባቸውንም ፡ ፍጥረት ሁሉ ፈጠረ። በመንፈሱም አጸናቸው።

የወጥ ማጣፈጫው ምንድር ነው ጨውና ቅመም ቅቤም ነው። የሰውም ማጣፈጫው ሃይማኖትና ፍቅር ነው። ሃይማኖት ያለው ሰው ሁሉን ያዝዛል ኤልያስ ሰማይን ሶስት ዓመት ከ፮ ወር ዘጋ ዝናብም አልዘነበም። ቀለም በቀንድ (በብልቃጥ) ሳለ ጨለማ ነው በተጽፈ ጊዜ ግን ብርሃን ነው።

ቀለም በቀንድ ሳለ ድዳ ነው በተጻፈ ጊዜ ግን መላሰኛ ነው። ቀለም በቀንድ ሳለ ጭምት ነው በተጻፈ ጊዜ ግን እንደሰከረ ነው። ሁሉንም ይለፈልፋል።

የንጉሥም ልጅ እንደዚህ ነው።

የዚህን ዓለም ሥሩን አገኛለሁ ብዬ ቆፈርሁት ጽኑም ድንጋይ ሆነብኝ ድጅኖ አሳቤም ሁሉ አለቀ እንዲያውም ባየው ባስተውለው ሥሩ እግዚአብሔር ነው።

ጨረቃ አንድ ጊዜ እንድትጎድል አንድ ጊዜ አንድ ትሞላ የዚህም ዓለም ንብረት እንደዚህ ነው ፀሐይ ሙሉ እንደሆነች ብርሃኗም ሙቀቷም የወዲያውም ዓለም እንደዚህ ነው። የሰው ልቡ ፊደል ነው ያሰበውንና የተናገረውን የሰማውንም ለቅሞ ይኖራልና።

እሳት ንጉሥ ነው ጢስ ጭፍራ ነው እሳት ንጉሥ ቢያቃጥል ጢስ ጭፍራ ያፍናል።

ከቡላድና ከድኝ ከእንጨትም እሳት ወጥቶ እንዲቃጠል ጻድቃንም ቢቆጡ እሳት ይዘንማል። ሙሽራ በጫጉላዋ ውስጥ እንደምታምርና ደስ እንደምታሰኝ ጻድቃንም በመንግሥተ ሰማያት እንደዚያ ናቸው።

ጸሐፊ ሰው የማትረባውንና የማትጠቅመውን ደብዳቤ ጠቅልሎ ከእሳት እንደሚጥል እግዚአብሔርም ይህን ዓለም ሲያልፍ እንደዚያ ነው።

በኖኅ ጊዜ የነበሩ ሰዎች ስለ ዝሙት አልተወደዱም ወሀ ሆነው ቀሩ እንጂ በሰዶም ዝሙት ግን የሎጥ ሚስት ጨው ሆና ቀረች።

ፀሐይ ለኢያሱ ስለምን ቆመችለት መድኃኒቱን ኢየሱስን መስሏት ይሆን ኢየሱስ መድኃኒቱ ሰውም አይገድል ያድናል እንጂ።

መድፍ ሽክሙ የከበደው ነው። ነገር ግን በመንኰራኵር ይሄዳል። ሰልፍም ለጊዜው የሚያስፈራ ግሩም ጭንቅ ነው። ማሸነፍ ግን በሀብት ነው እንጂ በጉልበት አይደለም።

በለዓም እሥራኤልን ለመርገም ለምን ይሄዳል ምርቃትን ያዕቆብ ሠርቆ እንዳመጣት አያውቅምን አህያዪቱ እንኳ ከለከለችው ለካ በጊዜው

መሥረቅ መልካም ነው። ኮከብ ከያዕቆብ ሲወጣ አየሁ ይላል ያዕቆብን ሰማይ ማድረጉ ነውን።

ባላቅስ በጉን ለምን በየተራው ይፈጃል ያዕቆብ እንደሆነ የበግ ለምድ ለበሰ። ቀስ ብሎ ገብቶ ከኤሳው የነጠቃት ምርቃት ናት።

እንዲያውስ ፈጣሪውን ሌሊት ሁለት ጊዜ ታግሎ የጣለ አይደለምን ፈጣሪውን ያሸነፈውን እኔ እችላለሁ ብሎ ነውን ደግሞስ ያማቱን በጎች እንጨት አዝጎርጉሮ እያሳየ ገና በማሕፀን ሳሉ ዝጉርጉር እያደረገ ለቅሞ የወሰደበት እርሱ አይደለምን ወንድሙንስ ገና በማሕፀን ስላእ ያስነካከለ እርሱ አይደለምን ባላቅ ሆይ ተው ይህ ሰው ረቂቅ ደጅን ይኖረዋል ልያስ ከራሄል ጋራ ምን ያጣላታል ወይስ እንደ ሎጥ ሚስት ጨው መሆን ይፈልጋታልን ፡ ስለ ዝሙት ይልቅ በልጅዋ እንኮይ መግዛት ይሻላታል ሎጥ ልጆቹን የደገማቸው እንደ እናታቸው ጨው ይሁኑ ብሎ ነውን።

# መጽሐፈ ጨዋታ ወንጌላዊ።

## ክፍል ፪።

እግዚአብሔር በደብረ ሲና በጁ አሥር ነገር ዘራ የሚያጭደውም በታጣ ጊዜ አንድ ልጁን ቢልከው እንግዳ ነውና በዳዊት ቤት አደረ ይህንም አዝመራ ፴፫ ዓመት ሙሉ ብቻውን አጭዶ በጨረሰ ጊዜ አባቴ አባቴ አመስግነኝ አለ ፡ ምነው ከረኛ ቤት ተወለደ ብለን አምተነው ነበር ፡ አሁንስ እርሱ ራሱ እረኝነቱን ገለጠው ለካ የበጎች እረኛ እኔ ነኝ እያለ ከሰማይ ተሰዶ የመጣ በጎችን ሊጠብቅ ነውን።

ከሰማይ ድረስ መጥቶ በግ መጠብቅ ካልቀረለት ይህችን ታናሽ መንጋ መጠበቁ ለምንድር ነው ከምድር ዳር እስከ ምድር ዳር ድረስ ያለውን መንጋ አንድ አድርጎ ጠብቆ ደመወዙን በምስጋና አውጥተን አንሰጠውምን።

የተሰበረውን ጠግኖ የደከመውን አሳርፎ ተኩላ እንዳይነጥቃቸው ጠብቆ ከበጎቹስ መልከካሙን እየመረጠ አይወስድምን። ቀበሮውንስ ያውቀው የለምን አንድ በግ ባገኘ ጊዜ ይዞ ወደ ጉድጓድ እንደሚገባ።

ያችም በግ ከረኛዋ ፈቃድ ወጥታ ከተገኘች መዳን የላትም። ምነው እርሱ ባዘዛት ብትገባ ደጁ እርሱ አይደለምን። አዳምንና ሔዋንን የኃጢአት ብርድ ቢያንቀጠቅጣቸው ክርስቶስ ሥጋን ለበሰ።

በበረትም ወድቆ ወገኖቹ የላም እረኞች አዩት ሰላም እረኞችም የምስራች ነገራቸው ለካ እረኛ እረኛ ነው።

## ክፍል ፫።

በ፭ሺ አምስት መቶ ዘመን እግዚአብሔር እጅግ ተዋረደ ፡ አንድ ልጁን ለሰው ባሪያ ሆነህ ሥጋ ተሸከም ብሎ ሰደደው። ወዮ ወዮ ዋ ዋ ዋ መላእከትስ ጌታ የሰው ሥጋ ሲሸከም እያዩ ቆመው ዝም ብለው ማየታቸው ለምድር ነው። የሥጋ ሙብል ስለአለበት ሁሉም የምድሪቱን ኑሮ ወደዱ። በሰማይስ ሥጋም ጠጅም የለም አሉ። እንደዚህ ያለ ባዶ አገር መላእክትን እከክ አይቆራርጣቸውምን።

የእግዚአብሔርስ ልጅ ከአባቱ ጉያ ተለይቶ የመጣ ለሥጋ ጓጉቶ አይደለምን። ከሰማይ ድረስ ተሰዶ መምጣቱ ሀብት ሆኖት መቸም አንድ ጊዜ ብላ ብሎታል። ዕለቱን እንደመጣ ከዳዊት ቤት በሥጋ አደረ።

ምነው አብና መንፈስ ቅዱስ ቀሩ። ሥጋ አያምራቸውምን እንኳን ልጅ ለሥጋ ስሱ ስለሆነ ተቅለብልቦ መጣ እንጂ ሁለቱስ እሳት ናቸው። ጥበባቸውም አይታወቅም። ይልቁንስ ልጅዮው ዘመዳችን ነው። ሁሉንም አጫውቶናል። የርሱስ ዝምድና ምንድር ነው የዚያው ልጅ ከዚያው ነው ዘረው ዘረው አንድ ናቸው። ብሎም የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል እንዲሉ ሁሉንም እናምናቸዋለንና አይተውንም።

## ክፍል ፬።

ማርያም ሰማይን መስለች ከቶ እሳቱ አጥቁሯት ይሆን። አይሁድ ቀን ሆኖ ሳለ በምድር ሲሄዱ የተናቀው ደንጊያ እንቅፋት ሆነባቸው ምነው አስተውለው ቢሄዱ። ኒቆዲሞስ ግን በሌሊት ሲሄድ በውሀ ውስጥ መንገድ አገኘ። ወሀም አ፭ሺ ከ፭፻ ዘመን መክና የነበረች አሁን ከእግዚአብሔር ልጆች ወለደች።

ከቶ ልጅነት አይቀርም ኢየሱስ ከዮሐንስ ጋራ አጫወት ብሎ ከዮርዳኖስ ባሕር ላይ ወደቀ በርሱም ድንጋጤ ሰማይ ተከፈተ። አባቱም

ከላይ ሆኖ ልጄ ወዳጄ ሲል ዋለ። መንፈስ ቅዱስም ርግብ ሆኖ በራሱ ላይ ዋለ። ዮሐንስ እነሆ የእግዚአብሔር በግ እያለ ለምን ያሳየዋል ያለጊዜው ይታረድ ብሎ ነውን። ቢታረድስ የታደሉና የመረጡ ጀግኖች ይበሉታል እንጂ ፡ ፈሪ አይበላውም። እርሱም ምሥጢር አይችልም ብናብለላውና ብናጠጣው ካባቱ ዘንድ ያየውን ሁሉ ነገረን።

ለቀበሮች ጉድጓድ አላቸው ለሰማይ ወፎችም ማረፊያ ዛፍ አላቸው ለሰው ልጅ ግን እራሱን የሚያስጠጋበት የለውም ይላል። ለካ ሰማይና ምድር ቢጠበው ነው ከሰው ውስጥ መጥቶ ያደረ እንደባሪያም የመሰለ።

ኢየሱስ ሥርግ ቢጠሩት በቃና ዘገሊላ ወህውን ጠጅ አድርጎ አጠጣ በሰው ሥርግ እንደዚህ የሆነ በራሱ ሥርግ እንዴት ይሆን። የእግዚአብሔርን ልጅ ሥርግ አይቼ ከድግሱም በልቼ ጠጥቼ ከዚያ ወዲያ ምነው በሞትሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ኑ ያባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን ውረሱ ይላል ዓለም ሳይፈጠር ምን ኖሮታል ጥበቡ አይታወቅም።

## ክፍል ፫።

እናንት የዓለም ብርሃን ናችሁ አለ መብራት አብርቶ በእንቅብ ውስጥ የሚያኖር የለም ይላል። ዓለምን ያህል እንቅብ ደፍቶብን የለምን እኛ በወዴት አናብራ። ጳውሎስስ እንኳ እስከ ዕድሜው ልክ አበራ።

አንተ ነጋዴ እያላችሁ ለምን ትሳደባላችሁ ገበያ ተደመቀ ምን ደኅና አለ ከእግዚአብሔር የበለጠስ ምን አለወጠውምን ፡ ቢያመቸው ፩ ልጁን ለዓለም አለወጠውምን ፡ ዮሴፍንስ ወንድሞቹ ለ፴ ብር አልሸጡትምን ከተሸጠ በኋላ ግን ለምድረ ግብፅና ለከነአን አገር የራብ መድኃኒት ሆነ።

አንበሳ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ዱር ገባ ምን እንስሳ ይሰብር ይሆን ከዲያቢሎስ በቀር። እነዚያ አራቱ መላእክት ፍም መጥቶ ተሰው ላይ

ሲወድቅ አለመናገራቸው ከነዚህስ ገብርኤል ይሻላል ተሽቀዳድሞ መጥቶ ለቆንጆዪቱ የነገረልን።

የሰማይ እሳት ከሰው ላይ ወድቆ አለማቃጠሉ ምንድር ነው። ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር የሥራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ልጅስ ገንዘባችሁን እየሰበሰባችሁ ወደ ሰማይ ላኩ ከዚያ ይቆያችኋልና ይለናል። ለካ የርሱ ገንዘብ አልበቃው ቢል ወደኛ ልጁን የላከ ቀስ ብሎ ገንዘባችንን በብልሀት እንዲያከማች ኖሯል። እንግዲህ አውቀንበት ገንዘባችንንም አናባክን ከሰማይስ እኛ ምን አለን ገንዘባችንንም አናባክን ከሰማይስ እኛ ምን አለን ገንዘባችንን ወደዚያ አሸከመን ከምንልክ አንካሶችን እውሮችን ችጋረኞችን ወንድሞቻችንን ይዘን እንከት እያደረግን እንበላዋለን እንጠጣዋለን እንለብሰዋለን በገዛ ገንዘባችን ምን ይመጣብናል። አለመጣችሁም ብሎ የሚያደርገውን እስቲ እናያለን።

አባቶቻችንን ከዚህ ቀደም አታሎ ያወጣው ገንዘብ ይበቃዋል ባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ገመል በመርፌ ቀዳዳ መሔድ ይሻላል ይላል። ከርሱ የበለጠ ባለጠጋ አለን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ይኖር የለምን ይህንን እያመካኘ የሰው ገንዘብ አሻግሮ ማየቱ ምንድነው ፡ ከዚህ ቀደም አሥሩን ተናግሮ ተናግሮ ከወንጌል አደረሰን አታስቡ እያለ ገንዘባችንን ሊያስበላብን ወዲያው ተርቤ አላበላችሁኝም። ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም። ታርዤ አላለበሳችሁኝም። ታምሜ አላሳያችሁኝም። እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም። ታሥሬ አልጠየቃችሁኝም ይላል። ይህን ያህል ስድስት ቃል ምን ያናግረዋል። ወዲህ ለነገ አታስቡ ይላል ወዲህ አላበላችሁኝም ይላል። ከኛ ወገን የተራበ የተጠማ ፡ የታረዘ የለም መስሎት ይሆን ተሰማይ ተሰዶ መጥቶ ተርቤአለሁ ተጠምቻለሁ ፡ ታርዣለሁ። ምንድር ነው ሰማይን ያህል ሰፊ አገር ይዞ፥ አባቱ ከዚያው አያበላውም አያጠጣውም አያለብሰውም ፡ ልጁስ ሲቀላውጥ ነውር አይፈራምን። እኛስ ለሰማይ ንጉሥ ልጅ አናበላም አናጠጣም አናለብስም

ከዚህ ካሉት ከድሆች ወንድሞቻችን ጋራ ገንዘባችንን ተካፍለን እንበላለን እንጠጣለን እንለብሳለን።

እንደዚህ ያለ ዘወትር ንዝንዝ ምንድር ነው። በወንጌል ገንዘባችንን ሊወርስም የጦር አዳር እያለ ሊከፈለን አስቧል መሰል።

## ከፍል ፯።

እግዚአብሔር ፈሪ ነው እኛ ብንበድለው ልጁን ልኮ ቀስ ብለህ ተዛምደህ ና ብሎ በልጁ ታረቀን አሁን ምን ያደርጉኝ መስሎት ነው ለካ በየቤቱ ፍራት አይታጣም እኛ ስለበደልነው የምንከሰውን እርሱ ካሰን።

እንግዴህ ወዲህ ሥጋችን ከሆነ በሰበብ ባስባብ ብለን እርስቱን እንካፈለዋለን ጥቂት ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ እንደሚሉት እንኳን ልጁን ልኮ ተዛመድን።

የክርስቶስ ነገር እጅግ አስቸገረ ፡ ልጅ ስለሆነ ይሆን አንድ ጊዜ ተርቤ አላበላችሁኝም ይላል አንድ ጊዜ አምስት እንጀራ ለአምስት ሽህ፥ ሰው አብልቶ አትርፎ ያስነሳል።

ለበሬ ቀንድ አለው ለንጉሥም ዘውድ አለው እረ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ክብር ምንድር ነው አንለይለትምን ፡ አምልኮ ስግደት ምሥጋና ለርሱ ነው በጣም አንገዛው አንለማመጠውም። አንታጠቅለትም። ታላቅ ጌታ ሰጭ ነሽ ነውና።

አዳኝም ገዳይም እርሱ ነውና። በሰማይና በምድርም ከርሱ በቀር ሌላ የለም። ሁሉም ከርሱ ነው የተገኘው ሁሉም የሆነው በርሱ ነው። አለ ርሱ ምንም የሆነ የለም ምስጋና ይገባዋል ለዘለዓለሙ አሜን።

እግዚአብሔር ዕሩቅ ነው ጥበቡ አይታይምና እግዚአብሔር ቅርብ ነው ቶሎ ይሰማልና። እግዚአብሔር መኰንን ነው ቶሎ ይፈርዳልና። እግዚአብሔር እንግዳ ነው ቶሎ ወሬ ይሰማልና። እግዚአብሔር ትሑት

ነው ፡ ሰውን አይንቅምና። እግዚአብሔር መሐሪ ነው ቶሎ ይቅር ይላልና ርኅሩኅ ነው።

እግዚአብሔር ሐኪም ነው። ሁሉን በጥበብ አድርጓልና እግዚአሔር ምስጉን ነው ፀሐይን ጨረቃን ፈጥሮአልና። እግዚአብሔር ክቡር ነው ሰማይና ምድር የርሱ ናቸውና።

እግዚአብሔር ባለ ጸጋ ነው ለሁሉ ይመግባልና። እግዚአብሔር ረቂቅ ነው አይጨበጥምና። እግዚአብሔር ግዙፍ ነው በዓለሙ ሁሉ ሞልቷልና። እግዚአብሔር ብሩህ ነው ጨለማ የለበትምና። እግዚአብሔር ኃያል ነው የሚቋቋመው የለምና።

እግዚአብሔር እሳት ነው እጅግ ያስፈራልና። እግዚአብሔር መካር ነው መጻሕፍትን ሰጥቶናልና። እግዚአብሔር አባት ነው አሳድጎናልና። እግዚአብሔር ወንድም ነው ሰው ሆኖዋልና። እግዚአብሔር ወዳጅ ነው የሆዱን ነግሮናልና።

እግዚአብሔር አገር ነው እንኖርበታለንና። እግዚአብሔር ማርና ሱካር ነው ይጣፍጣልና። እግዚአብሔር ገናን ነው የሚያህለው የለምና። እግዚአብሔር ትልቅ ነው ስፍራ አይበቃውምና። እግዚአብሔር ጥልቅ ነው በዋና አይገኝምና። እግዚአብሔር ፋሲካ ነው ለሁሉ ታርዷልና። እግዚአብሔር ዓመት በዓል ነው። ለሁሉ ደስታ ነውና። እግዚአብሔር ጨው ነው ሁሉን ያጣፍጣልና። እግዚአብሔር ክረምት ነው ሁሉን ያበቅላልና። እግዚአብሔር አይጠረጠርም ሁሉን ያውቃልና። እግዚአብሔር አይዘነጋም በሁሉ ድካም የለበትምና። እግዚአብሔር አይሰጋም የሚሸረው የለምና።

እግዚአብሔር የሰው ሎሌ ነው በክረምት ለማብቀል በበጋ ለማብሰል የተዘጋጀ ነውና። እግዚአብሔር እንግዳ አይደለም ከጥንት የነበረ ነውና።

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ጥንት ለነበረ አሁን ሳለ ኋላም ለሚኖር አሜን።

## ክፍል ፯።

ኢዮብ መከራ ቢታገስ ለራሱ ብዙ ዕድሜ ፡ እጥፍ ገንዘብ አገኘ። ክርስቶስ ግን ያንን ሁሉ መከራ ቢታገስ ለኛ ጥቅም ነው እንጂ ለራሱ አይደለም። ሶምሶን በሶስት መቶ ቀበሮ ጅራት እሳት አቆራኝቶ የፍልስጥኤምን አዝመራ አቃጠለ። ክርስቶስ ግን በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን አቆራኝቶ ዓለሙን ሁሉ አንድ አድርጎ በፍቅር እሳት አቃጠለ።

የእግዚአብሔር ልጅስ እጅግ ቀላ ሥጋ መሰለ እውራኑም እያዩ ደንቆሮዎችም እየሰሙ አንካሶችም እየሮጡ አደነቁት።

ክርስቶስ በደብረ ታቦር ላይ ቢለውጥባቸው ሁሉም ወደቁ። ጴጥሮስም ይወለፍት ጀመር ይህ ባላገር አምላክን አይቶት አያውቅ ይሆን አምላክን አይቶ እንደዚህ የፈራ ሌላ መከራ ቢመጣበት እንዴት ሊሆን ነው።

የፍቅር ምንጭ ማነው ክርስቶስ ነው። አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ለተራቡ ሥጋውን አብልቶ ደሙን አጠጥቷልና። አይሁድ ጦማቸውን አጥርተው ይጦማሉ ክርስቲያኖች ግን ጦማቸው የጠራ አይደለም ዓርብ የታረደውን የበግ ሥጋ ይበላሉና። አይሁድ ከእንስሳ እንኳ ለይተው ነው የሚበሉ ክርስቲያኖች ግን ወንድማቸውን ይበላሉ።

ዮሐንስ፥ እነሆ የእግዚአብሔር በግ ቢል አይሁድ ላይበሉት ተሽቀዳድመው አረዱት። እነሆ አይሁድ ያረዱትን በግ አሕዛብ እየበሉ ወፈሩ ቁመታቸውም እስከ ሰማይ ደረሰ። እስራኤል ግን ኮስሰው የማንም መጫወቻ ሆኑ።

መጽሐፍ አንድ አንድ ጊዜስ አያውቅም ሰው ቢሞት ደስ አይበልህ ይላል። ክርስቶስ ባይሞት ለኔ መንግሥትን ማን ይሰጠኝ ኖሯል። የርሱ ሞት እኔን ጠቀመኝ እሰይ እሰይ እንኳን የሞተልኝ እልል እልል እንግዲህማ ሥጋውንስ ብበላው ደሙንም ብጠጣው ምነው። እኔን የመሰላችሁ ሁሉ ደስ ይበላችሁ። ዳዊት ይሁዳን አገሩን ምድረ እብዳ ትሁን እያለ ምን ያራግመዋል እርሱ ካልበላሁለት ብሎ ነውን እንደ ይሁዳ ያለ መልካም ነጋዴ የለም የዘለዓለሙን ምግብ በ፴ ብር ሸጠልን።

የእግዚአብሔር ልጅስ እጅግ አድርጎ በረታ ከአንዲት ሴት ሥጋ ነጥቆ ወስዶ መካከል በቀራንዮ ሰቀለው ወር አለማፈር።

እግዚአብሔር ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ከሙሴ ጀምሮ እስከ ነቢያት ድረስ ጮኸ ጮኸ የሚሰማውም ታጣ ቃሉም ታሠረ እንግዴህ በምኑ ይንገራችሁ።

## <u>ክፍል ፯።</u>

አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ እሳት ስሙ ሶስት ቢሆን ኪሩቤል ይጨንቁ እንጂ እኔ ምን እዳዬ መቸውንም አንድ እሳት ነው በሥጋዬ ጠቅልዬ ተሸክሜዋለሁ። ኪሩቤልማ በስም እንስሶች ናቸው እንጂ ጥቂት እንኳ ሥጋ የላቸውም። ይህን የማይጠፋ እሳት እንዴት ይችሉታል።

ኦሪት በጋ ናት አድርቃ አንድዳለችና። ወንጌል ክረምት ናት ሁሉን አብቅላለችና። ኦሪት እሬት ናት ሁሉን አምርራለችና። ወንጌል ግን ማር ናት ሁሉን አጣፍጣለችና።

በንጹሕ ሰው ልብ ምድኟ፥ አብ ይጣዳል ወልድ ይፈላል መንፈስ ቅዱስ ይገነፍላል። ኦሪት ጨረቃ ናት ወንጌል ግን ፀሐይ ናት ዓለሙን ሁሉ ሞቃ ታበራለችና። ኦሪት በትሀ ናት ወንጌል ግን ጥሩ ጠጅ ናት በልክ ለሚጠጣት ሰው ጤና ሕይወት ትሰጣለችና።

አሪት አበባ ናት ወንጌል ግን ፍሬ ናት ሁሉን ታጠግባለችና። ምን እበላ ምን እጠጣ ምን እለብስ እያለ ሰው ለምን ያስባል። አርባ ዓመት ለእስራኤል መናን ያበላ ለሰማይ ደመናን የከለለ ለኤሊ ድንጋይን ያለበሰ አምላክ ይነሣዋልን።

አሪት ገጠር ናት ወንጌል ግን ከተማ ናት ሁሉ ይገኝባታልና። ወርካ ከሥሩ እየወፈረ ከጫፉ እንዲሰፋ ቤተ ክርስቲያንም እንደዚያ ናት።

በሁለት አህያ ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም የገባ መድኃኒት ዓለሙን ሁሉ አዳነ።

ሙሴ አሥር ቃል ተናግሮ ሰውን ሁሉ አስፈጀ። ምነው ባልተናገረ የማይችለውን ነገር ሙሴ ባጠፋ ክርስቶስን ሥጋ ጥሬውን ይበሉታል። ምነው ይሆን ፊት ከሙሴ ጋራ ነበረ ብለው ነው ይሆን።

እግዚአብሔርስ ሰው ባጠፋ ባሥሩ አመካኝቶ አንድ ልጁን ቢያስገድለው አሁን ምን ተጠቀመ። አዳም አንደኛ እንዳንዱ ሆነ ያለውን እፈጽም ብሎ ነውን።

ክርስቶስስ ከሙሴ ጋር ቀድሞ ምክር ያለው መሰለ ሥጋውን ሲበሉት ዝም ይላልና እነዚያስ አራቱ ዙፋን ቤቶች ዓይን ብቻ ናቸው አያዩምን ጌታቸው ባህያ ላይ ተቀምጦ ኢየሩሳሌምን ያህል ከተማ ሲገባ እያዩ ዝም ይላሉሳ እንስሶች ናቸው።

መስቀል አይሁድን አጠፋ ክርስቲያንን ግን ጠቀመ አዳነ ንጉሡ ቈስጠንጢኖስም በመስቀል ታፍሯል ለካ መስቀል መልካም ነው እኔ ያስኰንናል ብዬ። አይሁድ ክርስቶስን ያጣሮች ያመንዝሮች ወዳጅ ብለው የአመት ለካ እውነት ነው። በአንድ ብርሌ ሽቱ ያመንዝራዪቱን ኃጢአት ፋቀላት። በቀኙ የተሰቀለውም ቀማኛ አቤቱ በመንግሥትህ አስበኝ ፡ ብሎ አንዲት ቃል ቢናገረው ከሰው ሁሉ አስቀድሞ ገነት አገባው።

አዳምንና ሔዋንን በገነት የሠረቁትን መልሶ አገባቸው እንደዚህ ያለ ጌታ መቸም አይገኝ ምነው በአራቱ ማዕዘን ቢሾም እንደዚህ ያለ ኃጢአተኛ ወዳጅ የሰውን ኃጢአት ሁሉ ተሸክሞ የማይከብደው ኃጢአተኛ የሆንህ ወዲህ ና። ኃጢአትህን የሚሸከም ክርስቶስ አለልህ። በዚህ ዓለም ገበያ የምትነግዱ የዓለሙን የኃጢአት ትብትብ የሚሸከም ሰው በቀራንዮ ቆሞላችኋል የናንተን ትብትብ የሚሸከም ሌላ የለም ተሸካሚ ለምን ትፈልጋላችሁ። ሌላው ግን ገንዘባችሁን ወስዶ ሸከማችሁን ያከብዳችኋልና።

## ክፍል ፱።

መላእክትስ ጠጅና ሥጋ አይወዱም ይህን ፡ ለሰው፥ ልጆች በሥጋ ሲያደላ አይተው ይሆን ምነው ጌታቸው ሲሰቀል፥ ዝም አሉ ጌታቸው ሲሰቀል ከቶ ወዴት ሸሹ ምናልባት እንደርሱ እንሞታለ ብለው ይሆን መንጋ ፈሪ በሰማይ ተሰብስቦ። ሰይፍን አስረዝሞ አስረዝሞ ቢቆሙት ካልመቱበት ምን ይሆናል የፈሪ በትሩ አሥር ነው።

ይልቅስ ሥጋ የበላው ጠጅ የጠጣው ጴጥሮስ ይሻላል የማልኮስን ጆሮ በሰይፍ የመነጠረው።

እንግዴህ መላእክት ከሥጋና ከጠጅ ያከልከሉ ጌታቸውን ብቻውን አስደድበውታልና።

ይልቁንስ ፀሐይና ጨረቃ ተሸልሞ መኖር ይገባቸዋል የጌታቸውን ራቁትነት ቢያዩ ብርሃናቸውን ሰውረዋልና ከዋክብትም ረግፈዋልና ክብር ይገባቸዋል። ሀያ ራቱ ቄሶችስ ወዴት ሔደው ነው ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ የቀበሩት። የጦር ቀን ያልሆነ ሎሌ ለመቼ ነው። መንጋ ቀጥቃጣ ሞት ፈሪ እንዲያውም እሪማቸውን ሁለት ይውሰዱባቸው።

ምድርስ እግሩ ጫማ አልነበረችምን እንዴት መቃብር ሆነችው። ወይ ጊዜ ለካ ንጉሥ ሰሎሞን ለሁሉ ጊዜ አለው ያለው እውነት ነው።

መቃብርስ አሁን ስም ሆነባት እንጂ አሁን ምን ሆናት እንደ አልዓዛር እንኳ ያራት ቀን እራት አልሆናት። ማርያም መግደላዊትም ለካ የዋህ ናት ሽቱ አዘጋጅታ እሬሳ ነው ብላ ልትቀባ የሄደች። ለእኅቷ ለማርታ እኔ ነኝ ትንሣኤ ሕይወት ሲል አልሰማችምን። ወይም ተነሥቼ ገሊላ እቀድማችኋለሁ ሲል አልሰማችምን።

የዳዊት ቤት ግልገል አንበሳ በሦስት ቀን ተነሣ። ሰላሳ ብር ለይሁዳ ደስታው ነው ለክርስቶስ ግን ጭንቀቱ ሞቱ ነው። ለክርስቲያን ግን መልካም ገበያ ጥቅማችን ነው።

ሙሴ እግዚአብሔርን ቃል አጽፎ በሣጥን ከተተ። የዚህ ዓለም ገንዘብ ይኖርን ብሎ ነው ወይስ ወንጌልን ባይሰማ ነው በሣጥን አትሰብስቡ ማለቱ። እነሆ የፍልስጥኤም ሰዎች ከነሣጥኑ ወሰዱለት። እኛስ በሥጋ ተዋሕዶ የእግዚአብሔርን ቃል በላነው። የእኛ ሳጥን ልባችን ሆዳችን ነውና ጳውሎስም ሣጥኑ እናንተ ናችሁ ብሎናልና።

አይሁድ ጅሎች ናቸው። ክርስቶስ ከሰማይ ወረድሁ ቢላቸው ከእንጨት ላይ ሰቀሉት ያውም እንጨት ከነአኻቴው መሰላል የሰማይ መውጫ ሆነ።

እግዚአብሔር ለዓለሙ ሁሉ አንድ በግ ሰደደ አምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን ለተራቡ። እናንተ ምእመናን ሥጋውን በልታችሁ ምናልባት ባይበቃችሁ ደሙን ጠጡት። አሪት ደም አትጠጡ እያለች ረሀብ ትሞታላችሁን ዛሬ ጠጥታችሁት ከሞት ዳኑና በኋላ ንስሐ ትገባላችሁ። እናንተ የዚህ ዓለም ነጋዴዎች ከዚህ ካንቺ በግ ሥጋ ተቀራምታችሁ ምነው ስንቃችሁን ብትይዙ።

## ክፍል ፲።

እናንተ የአዳም ልጆች በዚህ ዓለም ያላችሁ እነሆ የእግዚአብሔር በግ ወሀችሁን ሊጠጣ መጥቷልና በጣም ደሙን ምጠጡት ጤና ይሆናችኋልና አትልቀቁት።

ከሰማይ የወረደ ዓሣ ቤተ ልሔም የተገኘ። በብርብራ የዓለም ኃጢአት የስከረ ተይዞ በቀራንዮ ቢሰቀል ዓለሙን ሁሉ አጠገበ።

ሰይጣን በይሁዳ ልብ ገብቶ ክርስቶስን ቢያስገድል ምን ተጠቀመ። ገንዘቡን ሁሉ ተዛረፈ እንጂ ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን እንደሚሉት ሁሉ እርሱ እጅግ ተጐዳ እንጂ ማን ተጐዳለት ፡ ከገነት የዘረፈው ገንዘብ ሁሉ ተመልሶ ገነት ገባ።

ክርስቶስስ አንድ ጊዜ ሞቶ ከተነሣ በኋላ አርባ ቀን ሙሉ ማነን ይሰልሳል። ሰማይንና ምድርንስ መውደዱ ምንድር ነው።

ደግሞስ እሥሩ ፍቱ ብሎ ወደ ሰማይ መወጣቱ ይህንስ ያህል ሥልጣን ለሰው መስጠቱ በአሥር ቀንስ ጰራቅሊጦስን ልኮ በሰናኦር የተለዋወጠውን ቋንቋ ለሐዋርያት ገልጦ ማናገሩ ምድርን መውደዱ አይደለምን።

ይህንን ሁሉ እያደረገ መንግሥት ማስፋት ምንድር ነው። ተመልሶ ባልታወቀ ቀን ለመምጣት አይደለምን እናንተ ወንድሞቼ ምዕመናን የወንጌልን ሰላም ጥሩር አድርጋችሁ ሃይማኖትን ጋሻ ጦር ይዛችሁ ተሰልፋችሁ ቆዩት። ያለዚያ እሳቱን ለብሶ እሳቱን ጐርሶ ይመጣላችኋል በእሳቱ ላቦትም ያጠፉችኋል።

## ክፍል ፲፩።

ክርስቶስ አዳራሽ የተገኘ ለት ምን ብለን እንፈክራለን ወንድሞቼ ሆይ ተነሡ የሃይማኖትን ጥሩር ልበሱ የሰላምን ሰይፍ ታጠቁ ጽድቅን እናድናት ፡ ከዚህ ዓለም ዱር ገብታለችኛ ቆንጆዬቱ ቀንጠፋ ጠጁ ሥጋው ጌጡ ፡ ገመሮ ብሩ ኩራቱ ቀጋ ሆነው ሰውረዋታልና እየጣስናቸው እንሂድ ጽድቅን እናገኛታለንና። እሷን ይዘን ባዳራሹ ውስጥ ሳናፍር እንድንፈክር።

ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ትሏታላችሁ ነቢያትን ሁሉ የገደለች በመጨረሻውም ጌታዋን የሰቀለች አይደለችምን ትሠርቃለች ትቀጥፋለች ታመነዝራለች ከቶ ምንድር ናት። ለካ አንተ አታውቅትምን ባሪያ እኮ ናት አሉ እንደዚህ እመቤት መስላ የምትቀልጥብን (የምትኮራብን።)

አሁን ምን ይሆነኝ ብላ ነው። እንደዚህ ያለ ኩራት እመቤት እያለቻት አንድስ መልከ ቢስ አፈር መሳይ አሁን ባርነቷ አልታወቀብኝም ብላ ነውን እነሆ እመቤቷ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትም ፡ ያደረገችውን ሥራ ሁሉ ሰምታለች።

አሁን እንደ ፀሐይ እያበራች የመጣች ለት፥ ድምጧ ይጠፋል። ውሀ ለመሆን ለመቅለጥ ብላ ነው።

ከቶ ባሪያ ከባርነቱ አይወጣም። እንትጠፋ ባታውቀውን ይሆን።

ያችስ እመቤቷ ምን እንደዚህ አሰለቻት። ይህን ሁሉ ከፋት እየሰማች የወንጌልን ቃል እፈጽም ብላ ነው መታገስ።

ባይሆን አንድ ጊዜ መጥታ ባሪያዋን ቀጥታ ከኛም ጋራ ተገናኝታ ጌጧን ውበቱዋን ሁሉ ዓይተነው ተጨዋውተን ጠግበናት ተሰነባብተን ተመልሳ አትሄድምን።

እኛ ልጆቿ ሁለጊዜ ትምጣ ትምጣ እያልነ ጧትና ማታ አሁን ብንናፍቃት ብንጐመጅላት ምን ተጠቀመች አናሳዝናትም ይሆን እንደዚህ መጥናቷና መጨከኗስ ወልዳ ባታውቅ ይሆን።

ደግሞስ የመጣሁ እንደሆነ ከድተው ይይዙኛል አይሰዱኝም፥ ብላ ፈርታ ይሆን የፈራች እንደሆን ዋስ እንጥራላት። ዋሱንም ብትጠላ ታምለን ታስገዝተን። አይተናት ተጨዋውተን ተመልሳ እንድትሄድ።

ወንድሞቼ ምእመናን ሰው አይስማ ምለን ተገዝተን ኣንታላት። እናምጣትም በመጣችልን ጊዜ ግን ከጡቷ ስር ተሽጉጠን ተሽጉጠን ዝም ማለት አለመስደድ ነው።

ከዚያ ስፍራ መሐላና ግዝት አይደርስምና ከዚህ በኋላ እርሷን አስቀርተን እግዚአብሔር ያውቅልናል ምን ያገኘን ብላችሁ።

ጴጥሮስ ጳውሎስ መድኃኒት ያላቸው ይመስለኛል። የሞተውም የታመመውም ይነሣላቸዋልና እንደዚህ ያለ፥ ግርማ ከታብ ሰፍተው ይዘው ይሆን። እረ ገና ከታባቸውንማ ደኅና እንደሆነ እናውቀው የለምን ጴጥሮስስ ያለ ሁለት ከታብ። ጳውሎስስ ያለ አሥራ አራት ከታብ ምን ከታብ አላቸው እንኳን መድኃኒቱንስ በልተውታል በሆዳቸው ነው አሉ።

ጉጉት አሞራ ናት ፊቷም እንደ ድመት ነው። ድምጧም የከፋ ነው። መናፍቃንም መልካቸው እንደ ሰው ነው ሥራቸው ግን የሰይጣን ነው።

እንድርማሚት ያፊ ያሬድ የምትባል መልኳ ያማረ ነው ድምጧም የጣፈጠ ነው። እንደዚች ቤተ ክርስቲያንም በፍቅር ያጌጠች ያማረች የተሸለመሽ ናት። በርኅራኄም የተዋበች ናት ቃሏም ወንጌል ነውና።

ጉንዳን በደረሰበት እንደሚቆነጥጥ መናፍቃንም በደረሱበት ጤና የላቸውም።

ሰማይ ከዚያ ላይ ሆኖ አንጓቦብን የሚኖር ከቶ ምንድር ነው ቀን ፀሐይን ሌሊት ጨረቃን ከዋክብትን ተሸልሞ ዘወትር እኔን እኔን እዩኝ እዩኝ እያለ ያደክመናል ምነው የናቀን ድሆች ናቸው ብሎ ነውን ረሳው መሰለኝ የወትሮው እንዳይመስለው በላዩ የተቀመጠው ወንድማችን ነውና። እርሱም ተመልሶ አሁን ይመጣል። እንደዚህ የኮራ እንደሰም ለመቅለጥ ነው እንጂ ፊቱን እንዴት ያየው ይሆን ኩራቱም ምድር አሰለቅቆታል። ምን ይሆናል እንደሚያልፍ አያውቅምን።

ምድርንስ ተገዢአቸው ቢላት ገደልና ዱር ባሕርም እየሆነች ለምን ታውከኛለች።

ደግሞም እግዚአብሔር አንድ ልጁን አስተምራት ብሎ ቢሰድላት ልጁን አስደብድባ አስገደለችውና ዋጠችው ጤናም አልሆናት በዋጠችው በሶስተኛው ቀን አስታወካት።

ዳታንንና አቤሮንን መስሏት ሳታላምጥ ዋጠችውና ካስታወካት በኋላ እነሆ ከሰማይ ባባቱ ቀኝ ተቀምጧል። ወንድማችን መሆኑን አታውቅምን የታዘዘችውን ትታ ለሆዷ እውጥ እውጥ ማለት ምንድር ነው።

እስቲ እንደምን ትሆናለች ያ ወንድማችን የመጣ ለት እንደ ሰም ለመቅለጥ ብላ ነው እንጂ የሚያልፍ ኩራት አሁን ምን ይሆናል እንዲያው ቅለት ነው እንጂ።

ብርሃን ከፀሐይ ጋር ምን ያለማምጠዋል እርሱ አስቀድሞ ተፈጥሮ የለምን ነገር ግን ልደምስስህ እያለው ሆዱን ይከፋዋል እንጂ ዘመድ ናቸው።

ብርሃን ለእኛ ዘመዳችን ነው። ከፀሐይ ቀድሞ ስናየው ደስ ይለናልና ነገር ግን ፩ ክፋት አለበት ጨለማ ሲመጣ ትቶን ይሸሻል። በዚህ ዓለም ከቶ አንድ አንድ ክዳት ያለው አይታጣም። በጨለማ ጊዜ ጨረቃና ከዋክብት ባይኖር ጅብ በበላን ነበር።

ወሀን አንተ ባሪያ ብለው እጅግ ከፋው እንግዴህስ ይወቀው ከቶም አህያ ነው። የሁሉን እድፍና ጉድፍ ተጭኖ የሚሄድ ፡ ነገር ግን ልግመኛ ነው። ዓይኑ ሲያይ ቢጭኑበት መርፌ እንኳን ቢሆን ይጥለዋል።

በመርከብ አድርጎ ሳያይ ቢጭኑበት ግን ፩ ሚሊዮን የሚሆን መድፍም አይከብደው።

ይህም ተንኮሉና ልግሙ አቅጥኖት ይኖራል። ሀብቱም ወደታች ከመፍሰስ በቀር ወደ ላይ መውጣት የለውም። ፍጥረት ሁሉ በጉንጩ እንደዚያው አያውቅምን።

እሳትም ብረትን ሠርቶ ጋግሮ ቀቅሎ አብስሎ ሲያበላ ደግ ያደርጋል ሲቀርቡት ግን ይፈጃል ለእኛም አይገዛ። ስለዚህ እንዳይሞት እንዳይድን አድርገን ብናኖረው ይሻላል።

ወሀማ ባይኖርበት ይቻላልን። እርሱን እንኳ መከታ እየሰጠ ሲያነደው ሲያነፍረው ሲያጤሰው መርከብና ሠረገላ ሲያስጐትተው ባቡር ሲያስነዳው ሲያስወቅጠው ሲያስፈጨው ይኖራል።

ወሀም በክረምት በክረምት ዘመዳችንን ይወስዳል በበጋ ደግሞ ጥሩ ነው ብለን ከሆዳችን ስናገባው የሰውነታችንን ልክ ይመረምርና ይኮራል።

እንግዲያውስ ጠጅ በጥባጭ አይደለምን ጌሾና ጠዶ ይቆራኙት።

ነገር ግን ጨርሰን አንጥላው። እንዶድ እንደሚቀላቀል ጌታችንም መንፈሱን በውሀ ቀላቅሎ አጥቦናልና።

ፀሐይ ምንም ዘመኗ ብዙ ሆኖ ለቆላ ኮምጣጣ ብትሆን ለደጋ በተሀ ናት። ቆላ ምን ባደረገ ከመጠጠችበት ይሆን። ቢርቃት ቢሸሻት።

ደጋማ ሁል ጊዜ ቀርቦ ይለማመጣታል እረ ገና ዘወትር በረዶ ሲፈላበት እያየች ዝም ትለው የለችምን አይደለም ስታኮርፈው ጊዜ ነው እንጂ ባታኮርፈውስ አንድ ጊዜ ወጥታ ታቀልጥለት ነበር።

ጨረቃና ከዋክብትስ መሞቅ የለ ሁል ጊዜ መቀዝቀዝ ምንድር ነው። ሰማይ የለም ይሆን ተሰብስበው ፀሐይን የማይዘርፏት መንጋ ፈሪ በሰማይ ተሰብስቦ።

ደመናም የታዘዘው ዝናም ሊያዘንም ታዘዘ እንጂ እንዲያው በድንገት እየመጣ የሚያፍነን ምን፥ ባልነው ነው።

ነፋስስ እኛን ለመግደል ነው የታዘዘ። አሁን ግንብ ሠርተን መውጫ መተንፈሻ ባሳጣነው።

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ቀድሞ የነበረ አሁንም ያለ ኋላም የሚኖር አስጀምሮ ላስጨረሰን ክብር ይግባው ለዘለዓም አሜን።